Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ስለ ኮቪድ/COVID-19 Comirnaty (Pfizer) ክትባት መረጃ

ወቅታዊ የሆነበት ቀን 15 መስከረም/September 2021 ዓ.ም

## ስለ ክትባቱ

ኮሚርናትይ/**Pfizer** ክትባት ሲሆን ሰዎች በኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ እንዳይታመሙ ይከላከላል። ሁለት መጠን/ doses ክትባቶች እንደሚያስፈልግ ብዙጊዜ በ3-6 ሳምንታት ለያይቶ ይሰጣል ይህም ለየት ባሉ ሁኔታዎች ላይ የጊዜ ልዩነቱ ረዘም ያለ ሊሆን ይችላል። ፕፊዘር/Pfizer ኮቪድ/COVID-19 ክትባት በህይወት ያለ ማንኛውንም ቫይረስ እንደማያካትት እና እርስዎን ለኮቪድ/COVID-19 አጋልጦ መስጠት አይችልም። ይህ በSARS-CoV-2 ቫይረስ ጠቃሚ የሆነ አካል፤ ስፒክ ፕሮቲን/spike protein ለተባለ ጀነቲክ ዝርያ ያካተተ ነው። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ሰውነትዎ አንድ ዓይነት የሆነ ስፒክ ፕሮቲን/spike protein ይፈጥራል። ከዚያም የርስዎ በሽታ መቋቋም አሰራር ለኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ ምክንያት የሆነን SARS-CoV-2 ቫይረስ እንዲዋጋው ትምህርት ይሰጣል። የጀነቲክ ዝርያ ኮድ በሰውነት በፍጥነት ይወገዳል።

ክትባት መውሰድ በፈቃደኝነትና ያለክፍያ በነጻ ነው። ስለ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ ማንኛውንም አሳሳቢ ጉዳዮች ወይም ጥያቄዎች ካለ ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ከርስዎ የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ወይም ከአጠቃላይ ሀኪምዎ/GP ጋር መነጋገር ይችላሉ።

## የክትባቱ ጥቅሞች

እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ከኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ በመከላከል ላይ ፕፊዘር/Pfizer ክትባት ጥሩ ውጤት እንዳለው በጣም ግዙፍ በሆነ ክሊኒካል ሙከራ አሳይቷል። ሁለት ጊዜ መጠን/ doses ፕፊዘር/Pfizer ክትባት ለወሰዱ ሰዎች ክትባቱን ካልወሰዱ ሰዎች ጋር ሲመጣጠን በኮቪድ/ COVID-19 በሽታ ምልክት የመያዝ/symptomatic እድላቸው ከመቶ እስከ 95 እጅ ሊቀንስ ይችላል። እድሚያቸው 65 ዓመት ለሆናቸው እንዲሁም ለአንዳንድ ቀደም ሲል የቋሚ ህክምና ጤና ችግር ለነበረባቸው ሰዎች ውጤቱ ተመሳሳይ እንደነበር እና ይህም ቀደም ሲል በአንዳንድ የተረጋጋ ጤና ሁኔታዎች ስለሚኖር ነው።

ለኮቪድ/COVID-19 መከላከል ሥራውን የሚጀምረው የመጀመሪያውን መጠን/ dose ክትባት ከወሰዱ በኋላ በ2–3 ሳምንታት ጊዜ ይሆናል። አንድ መጠን/ dose ክትባት መውሰዱ አንዳንድ መከላከያዎችን ላይሰጥ እንደሚችል፤ ይህም ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደሚቆይ ነው። ሁለት መጠን/doses ክትባት መውሰዱ ከፍተኛ መከላከያን ይሰጣል። ማንኛውም የክትባት ዓይነት ከመቶ 100 እጅ ስለማይሰራ፤ ስለዚህ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ አሁንም በኮቪድ/COVID-19 ሊታመሙ ይችላሉ።

ክትባት ለወሰደ ሰው አሁንም በ SARS-CoV-2 ሊበከል ይችላል። ምንም እንኳን የበሽታ ምልክት ባይኖራቸውም ወይም መካከለኛ የበሽታ ምልክቶች ቢሆኑም ቫይረሱ ግን ወደሌላ ሰዎች መተላለፍ ይችላል። ይሁን እንጂ በአሁን ጊዜ አውስትራሊያ ውስጥ በሚጠቀም የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በወሰደ ሰው ላይ ካልተያዘ በቅርበት ግንኙነት የሚተላለፍ ቫይረስ በመቀነስ ላይ እንደሆነ ነው።

ለዚህ ነው ክትባት ከተወሰደ በኋላ ሌሎች የመከላከያ እርምጃዎችን ለመውስ መቀጠሉ አስፈላጊ የሆነው፤ እንደ:

- የአካል ርቀትን መጠበቅ
- እጅን መታጠብ
- የፊት መሸፈኛ ጭንብልን ማጥለቅ
- ለኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ እና በተለይቶ መቆያ እራስን ማግለል እንደ በአስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ አስፈላጊነት።

በሁለት ጊዜ መጠን/doses የፕፊዘር/Pfizer ክትባት ወስደው ከነበር፤ አሁንም በአካባቢ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣን የወጣ የምርመራ ቅድመ ሁኔታን ካሟሉ (ለምሳሌ፡ ትኩሳት፤ ሳል፤ የጉሮሮ ህመም) የኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ አለብዎት።

## ይህንን ክትባት ማን ነው ማግኘት የሚችል

እድሚያቸው ≥12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑት ሰዎች የፕፊዘር/Pfizer ክትባት ማግኘት ይችላሉ።

## ይህንን ክትባት ማን ነው ማግኘት የማይችለው

ለሚከተሉት ካለብዎት ይህንን ክትባት መውሰድ የለብዎትም:

- **አለመስማማት/anaphylaxis** (ከፍተኛ ለሆነ አለርጂክ ዓይነት ችግር) ቀደም ሲል ለነበረ ተመሳሳይ የ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም., Pfizer ወይም Spikevax (Moderna))
- **አለመስማማት/anaphylaxis በሆነ የክትባት ይዘት ጋር ከተጋለጡ በኋላ፤** ይህም ለፖልየታይሊን ግልይኮል/polyethylene glycol (PEG) ያካተተ
- **ማዮካርዲቲስ/myocarditis እና/ወይም** ፐሪካርዲቲስ/pericarditis ቀደም ብሎ ለተወሰደ የ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም., Pfizer ወይም Spikevax (Moderna)) አስተዋጽኦ ያደርጋሉ
- **ማንኛውም የተፈጠረ ከፍተኛ አንጻራዊ አስተዋጽኦ፤** ይህም ልምድ ባለው የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ወይም የህክምና ልዩ ባለሙያ ግምገማን በመከተል፤ ቀደም ብሎ በተወሰደ የ mRNA COVID-19 ክትባት መጠን/ dose (ይህም., Pfizer or Moderna) እና ያለምንም ችግር ለይቶ ማወቅ ያልደረሰ ይሆናል

## ክትባት ለመውሰድ ማስጠንቀቂያ

አንዳንድ የጤና ችግር ላለባቸው ሰዎች ተጨማሪ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልግ ይሆናል፤ ይህም ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ወይም በልዩ መማክርት ባለሙያ ክትትል ለማድረግ ለ 30 ደቂቃዎች መቆየት። የሚከተሉት ካለብዎት፤ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎት መናገር:

- ቀደም ሲል የ mRNA COVID-19 ክትባት መጠን/ **dose** (ይህም Pfizer ወይም Moderna) ንጥረ ነገሮችን ያካተተ ክትባት ሲወስዱ **አለርጂ ተፈጥሮ ከነበረ**
- **ሌላ ክትባት ወይም መድሃኒት ሲወስዱ አለመስማማት/Anaphylaxis ተፈጥሮ ከነበር።** የርስዎ ክትባት አቅራቢ ቀደም ብሎ ከወሰዱት የኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ንጥረ ነገሮች ጋር ተመሳሳይ ስለመሆኑ በማጣራት ማረጋገጥ
- በአሁኑ ጊዜ ህክምና የሚያስፈልገው፤ ከማስቶስይቶሲስ/mastocytosis ጋር ለታወቀ አለመስማማት/anaphylaxis ማሳወቅ ይሆናል።

**የመድማት ችግር ካለብዎት** ወይም **የደም ማቅጠኛ መድሃኒት** (anticoagulant) **የሚወስዱ** ከሆነ፤ ለርስዎ በሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ መናገር። ክትባቱን በጅማት ውስጥ መርፌ አድርጎ መውሰዱ ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆን አለመሆን ለማወቅ እንዲሁም ለመርፌው ጥሩ ጊዜን ለመወሰን የርስዎ በሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ሊረዳዎት ይችላል።

## ክትባቱን ከመውሰድ በፊት ለየት ላሉ ሁኔታዎች ለመነጋገር

### ለ Pfizer ክትባት ጥንቃቄ መውሰድ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች

ከዚህ በሚከተሉት የጤና ሁኔታዎች ታሪክ ላለባቸው ሰዎች ለፕፊዘር/Pfizer ክትባት ማግኘት ሲችሉ ነገር ግን ክትባቱን ለመውሰድ ስለ ጥሩ ጊዜ እና ተጨማሪ ጥንቃቄዎች ለመውሰድ ከአጠቃላይ ሀኪም/GP፤ ከበሽታ መከላከያ ክትባት ልዩ ባለሙያ ወይም ከልብ ባለሙያ/cardiologist ምክር ማግኘት አለባቸው:

- በቅርቡ (ይህም ባለፉት 6 ወራት) ወይም በቅርቡ የልብ ማቃጠል ህመም፤ ለምሳሌ። ማዮካርዲቲስ/myocarditis, ፐሪካርዲቲስ/pericarditis, ኢንዲካርዲቲስ/endocarditis
- የማይድን የቁርጥማት ህመም (ይህም ተግባራዊ ከማዮካድጊል/myocardial ማቃጠል ህምመ ጋር) ወይም የማይድን ከባድ የልብ በሽታ
- ከባድ የልብ መቆም ችግር ይሆናል።

### ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ላላቸው ሰዎች (immunocompromise)

ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ባላቸው ሰዎች የሚካተቱት የጤና ችግር ያለባቸውና የበሽታ መቋቋም አሰራር አቅም ለተዳከመ ነው፤፡ እንዲሁም ለበሽታ መቋቋም አሰራር አቅም የሚያዳክም መድሃኒቶችን ሰዎች ሊያካትት ይችላል።

ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ላላቸው ሰዎች የኮቪድ/COVID-19 ክትባት እንዲወስዱ የአውስትራሊያ መንግሥት በጥብቅ ያሳስባል። ፕፊዘር/Pfizer ህይወት ያለው ክትባት አይደለም። ይህ ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ላላቸው ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።

ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ባላቸው ሰዎች የሚካተት ከሄቻይቪ/ HIV ጋር ለሚኖሩ ሰዎች፤ በኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ የህመም ከፍተኛ ችግር ለሚደርስባቸው ሰዎች፤ ይህም ከፍተኛ የሞት ችግርን ያካተተ።

በፕፊዘር/Pfizer የተደረገ ክሊኒካል ሙከራዎች ውስጥ ለጥቂት ሄቻይቪ/ HIV ላላቸው ቡድኖች በስተቀር ለደካማ በሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ላላቸው ሰዎች አላካተተም። ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ላላቸው ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር የፕፊዘር/Pfizer ክትባት በጥሩ እንደሚሰራ አናውቅም። የፕፊዘር/Pfizer ክትባት በአጠቃላይ ህዝቡ ላይ እየሰራ እንዳለው ምናልባት ደካማ የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል ባላቸው ሰዎች ላይ መስራት አይችል ይሆናል። ሌሎችን የመከላከያ እርምጃዎች እንደ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የአካል እርቀትን በመጠበቅ መቀጠሉ ጠቃሚ ይሆናል።

### ለነብሰጡር ለሆኑ ሴቶች ወይም ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች

ነብሰጡር ለሆኑ ሴቶችና ታዳጊ ወጣቶች በማንኛውም የእርግዝና ጊዜ መደበኛ የፕፊዘር/Pfizer ወይም ሞደርና/Moderna ክትባት መሰጠት አለበት። ለማርገዝ ሙከራ ጥረት የሚያደርጉ ከሆነ፤ ክትባትን ለመውሰድ አለማዘግየት ወይም ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ እርግዝናን ማስወገድ።

ኮቪድ/COVID-19 ለያዛቸው ነብሰጡር ሴቶች ከባድ ህመም ከፍተኛ እንዲጨምር እና በእርግዝናው ላይ ተቃራኒ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። ትክክለኛ የዓለም ማስረጃ አገላለጽ እንደሚያሳየው ፕፊዘር/Pfizer ክትባት ለነብሰጡር ሴቶችና ለእናት ጡት ለሚያጠቡ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።

ጡት የሚያጠቡ ከሆነ የኮሚርናትይ/ Pfizer ክትባት መውሰድ ይችላሉ። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ጡት ማጥባቱን ማቆም አይኖርብዎትም።

### የኮቪድ/COVID-19 ታሪክ ላለባቸው ሰዎች

ቀደም ሲል ኮቪድ/COVID-19 ከነበረብዎት ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ ይናገሩ። በኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ ከባድ የማይድን SARSCoV-2 ህመም ላለባቸው ሰዎች ክትባቱ እስከ ስድስት ወራት መጠበቅ እንዳለበት፤ ይህም ባለፉት ብክለት በሽታዎች ችግር እንደገና መፈጠር የሚቀንሰው ቢያንስ 6 ወራት እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ እንዳለ ነው። ይሁን እንጂ ክትባቱን ለመውሰድ መጀመር የሚቻለው ከበሽታ ምልክቶች ሲያገግሙ ነው። በአንዳንድ ሰዎች ላይ ምንም እንኳን በሽታው ቢኖርባቸውም ከ6 ወራት ቀደም ብሎ ክትባቱን መውሰዱ አግባብ ሊሆን ይችላል። ከርስዎ ሀኪም ወይም የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ጋር መነጋገር። ከኮቪድ/COVID-19 ጋር በተዛመደ የማያቋርጥ ህመም ካለብዎት ክትባቱን ለመውሰድ ጥሩ ጊዜ መቸ እንደሆነ ከህክምና ሀኪምዎ ጋር መነጋገር ነው።

## ፐፊዘር/Pfizer ክትባት እና ህጻናት

ፐፊዘር/Pfizer ክትባት እድሚያቸው 12 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች እንዲጠቀሙበት የተሰጠ ጊዜያዊ ፈቃድ እንጂ ለታዳጊ ህጻናት መስጠት እንደማይቻል ነው።

## ለፐፊዘር/Pfizer ክትባት ደህንነት ስለማረጋገጥ

ለክትባት ምርመራ ጥናት የገንዘብ እርዳታን በመጨመር እና ለፐፊዘር/Pfizer እና ሌሎች ክትባቶች ምርመራ ጥናት በጣም ብዙ የፈቃደኛ ተመርማሪ ቁጥር መጠቀም እንደተቻለ እና በፍጥነት ሌላ የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች እንዲወጡ ተደርጓል። ታላቅ የክሊኒካል ሙከራ ላይ 44,000 የሚሆኑ ሰዎች እንደተሳተፉና የፐፊዘር/Pfizer ክትባት ድህንነቱ የተጠበቀና በጥሩ እንደሚሰራ ተገልጿል።

በህክምና ጥራት አስተዳደር (TGA) በአውስትራሊያ ውስጥ ላሉ ክትባቶች በሙሉ ፍተሻ ያደጋል። በዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው አንድ ክትባት ተቀባይነት እንዲያገኝ ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ፤ ጥሩ የሚሰራ እና በከፍተኛ ጥራት ደረጃ ያለውን ለማምረጥ በዚህ ይረጋገጣል። ለፐፊዘር/Pfizer ክትባቶች ማዘዣ አሰራር ሂደት በድረገጽ TGA website ላይ ይቀርባል።

የኮቪድ/COVID-19 ክትባት መስጫ ፕሮግራም በሚካሄድበት ጊዜ በኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ደህንነት ላይ ያለማቋረጥ ቁጥጥር ይደረጋል።

የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባትን ከወሰዱ በኋላ በጣም አነስተኛ የሆነ ችግር በደም መርጋት ላይ ከአነስተኛ የደም ፕላተለት/ platelet ቁጥር ጋር እንደተከሰተ ሪፖርት ተደርጓል። የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት የተሰራው በተለያየ መንገድ ነው። ከፐፊዘር/Pfizer ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ጋር በተገናኘ ማስረጃ የለም።

ሊከሰት የሚችል ለተጠረጠረ ችግር ለርስዎ በሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ወይም ለሌላ ለጤና ጥበቃ ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ ይቻላል። ከዚያም እርስዎን በመወከል መደበኛ ሪፖርት ለርስዎ አስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶርይ ጤና ጥበቃ መምሪያ ወይም በቀጥታ ለ TGA ሪፖርት ያቀርባሉ።

ሪፖርቱን በራስዎ ማቅረብ ከፈለጉ እባክዎ በድረገጽ TGA website ላይ መግባትና ከኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ጋር በተዛመደ ሊከሰት ስለሚችል ችግር ጥርጣሬ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል መረጃ ያገኛሉ።